# አብዮታዊ ዴሞክራሲ እየተሸረሸረ ነው

# አብዮታዊ ዴሞክራሲን ማዳን ማለት ኢትዮጵያን ማዳን ማለት ነው



ከሀዳሴ ኢትዮጵያ

ሚያዝያ 17፣ 2010 ዓ.ም.

hidaseethiopia@yahoo.com ወይም
hidaseethiopia@gmail.com

# Contents


1 መግብያ ..... 3

2 አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከባድ ፈተና ላይ ነው ..... 3

2.1 የጥልቅ ተሃድሶ አጀማመር እና አሁን ያለበት ሁኔታ ..... 5

2.1.1 ህወሓት ..... 5

2.1.2 ደኢህዴን ..... 6

2.1.3 ብአዴን ..... 6

2.1.4 ኦህዴድ ..... 7

2.1.5 አጠቃላይ እንደ ኢህአዴግ ..... 8

2.2 የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መሸርሸር ምልክቶች ..... 8

2.2.1 የቋንቋ ፖለቲካ ..... 8

ሀ. አማርኛ ለምን የአገራችን የስራ ቋንቋ ሆነ ..... 8

ለ. የፌደራል የስራ ቋንቋ ጥያቄና ተገቢነቱ ..... 9

ሐ. የቋንቋ ፖለቲካ መታረም አለበት ..... 10

2.2.2 የኢህአዴግ ሊቀመንበር ምርጫ ..... 11

2.2.3 የኪራይ ሰብሳቢነትን መታገል ያቃተው አመራር ..... 14

2.2.4 የጎራ መደበላለቅ ..... 15

- አብሮ የመስራት ጥሪ ..... 15
- በባንዲራዎቻችን ያለን እምነት መሸርሸር ..... 15
- እስረኞችን በመፍታት ላይ የተንፀባረቀው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መሸርሸር ..... 18
- በፓርላማ ውሳኔ አሰጣጥ የፀረ ሰላም አቋም መያዝ ..... 19

3 የአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስተር ብቃትና ተቀባይነት ..... 19

4 የአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስተር ፈተናና የመፍትሄ አቅጣጫ ..... 21

5 ማጠቃለያ ..... 22

**አብዮታዊ ዴሞክራሲ እየተሸረሸረ ነው፣**

**አብዮታዊ ዴሞክራሲን ማዳን ማለት ኢትዮጵያን ማዳን ማለት ነው**

# 1 መግብያ

የኢትዮጵያ ህዝብ ከሌሎች ፖለቲካ ፓርቲዎች አወዳድሮ ኢህአዴግን ሲመርጥ በመስመሩ /አብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም ልማታዊ ዴሞክራሲ/ ነው የመረጠው፡፡ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ የሚመራበት መስመር የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ነበር፣ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስተር ሃ/ማሪያም ደሳለኝ የሚመራበት መስመር የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ነበር፣ የአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስተር ዶ/ር አብዪ አሕመድ የሚመራበት መስመርም የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም ደግሞ ልማታዊ ዴሞክራሲ መስመር ነው፡፡

ልማታዊ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን ተቀባይነት ያገኘው፣ በተግባር ተፈትኖ ለውጥ በማስመዝገቡ ነው የኢትዮጵያ ህዝብ ምርጫውን ያደረገው፡፡

ይህን ፅሁፍ ለመፃፍ የገፋፋኝ ነገር አሁን በጥልቅ ተሃድሶ ላይ በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ውስጥ የሚታይ ያለውን ዥንጉርጉር፣ ወይን ደግሞ ወጥነት የሌለው አካሄድና ከተለመደው አካሄድ ውጭ የሚታዩ ጉዳዮች በመብዛታቸው ነው፡፡ በኔ አመለካከት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር እና እምነቶችን በመሸርሸር ላይ ናቸው የሚል እምነት በመያዝ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከአደጋ ለመከላከል ዴሞክራሲያዊ ትግል መደረግ አለበት፣ ዴሞክራሲያዊ ትግል ደግሞ ቦታና ጊዜ አይለይም፣ ስለዚ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እምነቶች እየተሸረሸሩ ይመስላሉ የምላቸውን ነጥቦች በማንሳት እንድንወያይባቸው በሚል ታሳቢ ነው ይህን ፅሑፍ የተዘጋጀው፡፡ ዋና አላማ ለአገር የሚበጅ ነገር አስተዋፅኦ ለማድረግ ነው፡፡

# 2 አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከባድ ፈተና ላይ ነው

ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት አገራችን ያስመዘገበችው ለውጥ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም የልማታዊ ዴሞክራሲ መስመር ውጤት ነው፡፡ ባለፉት 4-5 ዓመታት የታዩ ችግሮች ምክንያትም ገዢው ፓርቲ ወይም አመራሩ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመሩ ወጥቶ መጓዝ በመጀመሩ ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም የህዝቡን የልማት እና የመልካም አስተዳደር ጥማትን ማርካት አልቻለም፡፡ በመሆኑም የዚህ መገለጫ ኣብዛኛው በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ጥያቄውን የሚያቀርብ ቢሆንም ግን ደግሞ ዴሞክራሲው ገና ለጋ እድሜ ያለውና ያልጎለበተ፣ እንደ ባህል ያልተያዘ በመሆኑ ሃላቀርነት ተደምሮበት ወደ ብጥብጥና ሁውከት የገባ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ሰላም ወዳዱ ህዝብ በጊዜው ጥያቄው እየጠየቀ ቢመጣም ጊዝያዊ መፍትሄ እንጂ

መሰረታዊ መፍትሄ ማግኘት አልቻለም፡፡ ችግሮቹ ተደማምረው አሁን ላለንበት ደረጃ ደርሷል፡፡ ኢህአዴግ ይህን ችግር ለመፍታት ጥልቅ ተሃድሶ ሎኩሶ የማጥራት ስራው ከላይ ከአመራሩ ጀምሮ ወደታች ወደ ህዝቡ በመውረድ ላይ ይገኛል፡፡

ይሁን እና አራቱ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች በተመሳሳይ ደረጃ ተሃድሶውን እያንቀሳቀሱት አይደለም፡፡ በትክክል ውስጣቸውን ከመፈተሽ ይልቅ እርስ በርሳቸው መወነጃጀል እና አንዱን የአንዱን እርምጃ እያየ እየደመረ እየቀነሰ እርምጃዎችን መውሰድ የመረጡ ይመስላል፡፡ ለምሳሌ በኢህአዴግ የትግል ታሪክ ውስጥ ያልተለመደና ሁሉንም ያስገረመ ክስተት አንዱ በኦህዴድ የተደረገው የሊቀመንበር ለውጥ ነው፡፡ ከአሁን በፊት ይደረግ የነበረው አብዮታዊና ተራማጅ የኮር አመራር ስያሜ በትግል የተመሰረተ ሂደት በማለፍ ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን ያየነው በትክክለኛ ግምገማና የትግል ሂደት ያለፈ የተሃድሶ ውጤት ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱ የሰአታት ስብሰባ በማድረግ የተደረገ ሹምሽር ነበር፡፡ ሌላው ክስተት አብዛኛው የኦህዴድ የፓርላማ አባላት የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ውሳኔ /የኦህዴድ ሊቀመንበር ዶ/ር አብዪ አሕመድ የተሳተፉበት ውሳኔ/ በመቃወም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በመፃረር ድምፅ ሲሰጡ በሌሎች የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችና በአጋር ድርጅቶች አብላጫ ድምፅ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ሊፀድቅ ችሏል፡፡ ይህ ወጣ ያለ በኦህዴድ የታየ ቢሆንም በአጠቃላይ በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ያለውን የመበስበስ ደረጃ፣ መገለጫው ሊለያይ ካልሆነ በስተቀር በሁሉም ያለ ተላላፊ በሽታ ሆኖዋል፡፡ ኢህአዴግ ምንኛ ወደ ዝቅጠትና መበስበስ አደጋ መግባቱና የጎራ መደበላለቅ መከሰቱ ወለል ብሎ ይታያል፡፡ በተለይ አመራሩ ምንያክል ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር ወጥቶ ብዙ ርቀት የተጓዘ መሆኑ የሚያሳዩ ለዓመታት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ህልፈተ-ሞት ይመኙ የነበሩ ሃይሎች ሳይቀር የኢህአዴግ አመራር እና የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች በዘር፣ በፖለቲካ እምነታቸው በመለያየት አንዱን ሲያወድሱ አንዱን ሲያጥላሉ ይታያል፡፡

ሁሉም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ላለፉት 2 ዓመታት ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር ወጥተው በዝቅጠት አዘቅት ሲምቦራጩቁ ከቆዩ ቦኋላ የዝቅጠቱ ጥልቀት እየጨመረ ሲሄድ፣ አስተሳስሯቸው የነበረ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ገመድ /ባይበጠስም/ እየሳሳና እየላላ መሄድ ከጀመረ ረጅም ርቀት ሄዶዋል፡፡ ይህን የዝቅጠትና የመበስበስ ዓደጋ በኢህአዴግ ላይ እያንዣበበ መሆኑ አንዳንድ የቀድሞ የኢህአዴግ ኮር አመራሮች ሁኔታውን በመገንዘብ አስተያየት ቢሰጡበትም ሰሚ ጆሮ ሊያገኙ አልቻሉም፡፡ ያለውን ኮር አመራር ችግሩን አሳንሶ በማየት በግምገማ የሚፈታ እንጂ ብዙ አሳሳቢ አይደለም በማለት ላለፉት ሁለት ዓመታት በግምገማ ተከርሟል፡፡ በመጨረሻ አንዳንዶቹ በስራ ላይ ያሉ ኮር አመራሮች የችግሩን አሳሳቢነት መገንዘብ ሲጀምሩ፣ በኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ደረጃ አጀንዳ ሆኖ ወደ ዳግም ጥልቅ ተሃድሶ መግባቱ ይታወቃል፡፡ ጥልቅ ተሃድሶው የት ደረሰ?

## 2.1 የጥልቅ ተሃድሶ አጀማመር እና አሁን ያለበት ሁኔታ

ኢህአዴግ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ መርህ እየተከተለ ህዝብን አሰልፎ በመታገል ለድል የበቃ በውስጡ አራት ብሄራዊ ድርጅቶች ያቀፈ አንጋፋው ድርጅት ቢሆንም የውስጠ ድርጅት ትግል በመቀዛቀዙ ምክንያት የዝቅጠት ቀዳዳ ተፈጥሮ ቀስ በቀስ ወደ ዝቅጠት ሲገባ ሃይ ባይ ታጥቶ ቀላል የማይባል ርቀት ተጉዟል፡፡ ከአራቱም ድርጅቶች ማነው ቀድሞ የገባው/የተበላሸው የሚል አከራካሪ ቢሆንም ማንም ከደሙ ንፁህ የለም፡፡ በመሆኑም ባለፉት 2-3 ዓመታት ሁሉም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች በዝቅጠት አዘቅት ውስጥ ሆኖ የዋና ውድድር አስመስለውት ቆይቷል፡፡ ጎርፍ እያሳሳቀ ይወስዳል እንደሚባለው በዝቅጠት አዘቅት ውስጥ ሆኖ በውሸት ሪፖርት ራስን በማታለል እርስ በርስ በመሸላለም ብሎም በስካር መንፈስ እርስ በርስ በመነታረክና በመጣላት ዴሞክራሲያዊ መድረክ ጠፍቶ በሃሜትና በአይነቁራኛነት በመተያየት አብዮታዊ ዴሞክራሲ ለከፍተኛ አደጋ እስከማድረስ በቅቷል፡፡

ኢህአዴግ በዝቅጠት ባህር ውስጥ ሆኖ መዋኘት ላይ ቢሆንም፣ የህዝባዊ ወገንተኝነቱን እርሾው ገና ስላላለቀ፣ ለህዝብ ጥያቄ ተገቢውን መሰረታዊ መፍትሄ ባይሰጥም የእሳት ማጥፍያ ምላሽ ይሰጥ ነበር፡፡ በመሆኑም አንዴ ጥልቅ ግምገማ /2008 ዓ.ም./ ሌላው ጊዜ ጥልቅ ተሃድሶ /2009 ዓ.ም./ በማለት የጥገናዊ ለውጥ ለማምጣት በመሞከረ ነበር ያለፉት ሁለት ዓመታት ያሳለፈው፡፡ ሆኖም ግን የህዝቡ ጥያቄ ፋታ የማይሰጥ እና የዝቅጠቱ አደጋ እየተባባሰ በሚሄድበት ጊዜ በአመራሩ ውስጥ መከፋፈልና መጠቃቃት ሲጀምር ከኮር አመራር ውጭ ያለው የድርጅቱ አፍቃሪ ሃይልም ጫና ሲበዛ ሳይወደድ ወደ ዳግም ጥልቅ ተሃድሶ መግባት የግድ ሆነ፡፡ ዳግም ጥልቅ ተሃድሶ ከተጀመረ 7ኛ ወሩ ያደረገ ሲሆን፣ አሁንም እንደ ኢህአዴግ ሆኖ ሲታይ ገና አስተማማኝ ዋስትና ያለበት አይደለም፡፡ አሁንም የድረሱልኝ ጥሪ እያሰማ ያለ በቋፍ ላይ የተንጠለጠለ ተሃድሶ ነው፡፡ በእውነቱ እንነጋገር ከተባለ ጥልቅ ተሃድሶ ያለበት ደረጃ በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ ነው፡፡ በኔ እይታ በያንዳንዱ ብሄራዊ ድርጅት ጥልቅ ተሃድሶ ያለበትን ደረጃ ስመዝነው እንደሚከተለው ቅደም ተከተል ይሆናል፡፡

### 2.1.1 ህወሓት

ህወሓት በዝቅጠት ባህር ውስጥ ገብቶ ሲንፈራገፕ የነበረና ባለፉት ሁለት ዓመታት ከዚህ አዘቅት ላለመውጣት በግምገማና በጥልቅ ተሃድሶ ስም ራሱን ሲያሞኝ የህዝቡንና የአባሉን እሮሮ ጆሮ ዳባልበስ ሲል የቆየ ቢሆንም፣ በመጨረሻ ላይ ግን የትግሉ ሰማእታት ከእንቅልፉ እንዲባንን ስላደረጉት ቆራጥ እርምጃ በመውሰድ በያዝነው ዓመት /2010 ዓ.ም./ ባመዛኙ ከዝቅጠት ሜዳ በመውጣት ወደ ትክክለኛው የተሃድሶ ጎዳና ለመግባት

ከፍተኛ ትንቅንቅ በማድረግ ላይ ያለ ቢሆንም የግንባሩ /የኢህአዴግ/ ጉዳይ ጫና እየበዛበት ይመስላል በሚፈለገው ፍጥነት በመሄድ ላይ ችግር አለበት፡፡

ህወሓት ጥልቅ ተሃድሶ ያወጀው በ2009 ዓ.ም. ቢሆንም፣ ኔትዎርክ እና ክራስ ሰብሳቢነት ኮር አመራሩን አሳስሮ ወደፊት እንዳይራመድ እና ዓይኑን እንዳይገልጥ በማድረጉ ለከፍተኛ ጉዳት ተዳርጓል፡፡ በስተመጨረሻ ኮር አመራሩ ዓይኑን መግለጥ በመጀመሩ ቢያንስ የኔትዎርክ ገመዱ ለመበጣጠስ በቅቷል፣ በዚህም ምክንያት በክልሉ ህዝብ ከፍተኛ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ በኪራይ ሰብሳቢነት በኩል ግን ገና ብዙ ትግል ይቀረዋል፣ ህዝቡ በዚህ ላይ ትግሉ ተፋፍሞ እንዲቀጥል በከፍተኛ ጉጉት እየጠበቀ ነው፡፡ ህወሓት ከተሃድሰው ጎዳና እንዳይወጣ የአባሉና የህዝቡ ስሜት እና ፍላጎት የእሳት አጥር ስለሆነበት ባመዛኙ ወደ ዝቅጠት ይመለሳል የሚል ግምት ባይኖርም የግንባሩ ጉዳይ ግን በጣም ፈታኝ ፈተና እየገጠመው ነው፡፡ ስለዚ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ወደፊት ለማስቀጠል ከጦርነት ያልተናነሰ አስቸጋሪ ትግል እፊቱ ተደቅኖበታል፡፡

ህወሓት እንደ ቀድሞው ሁሉ ካለው በተነፃፃሪ ረጅም የትግል ዕድሜና ተሞክሮ አንፃር፣ ኢህአዴግ እንደ ድርጅት በጥልቅ ተሃድሶ ነበልባል ነጥሮ እንዲወጣ አብነታዊ ሚና እንዲጫወት እና አደጋላይ የወደቀው አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚጠይቀውን መስዋእት በመክፈል አርአያ ሊሆን ይገባዋል፡፡ አሁን ባለንበት ዘመን በዘመነ ኢንፎርሜሽን የሌላውን ልብ መማረክ የሚቻለው በንግግር ለማሳመን መሞከር ብቻ ሳይሆን፣ የምትናገረውን ራስህ ሆኖ በመገኘትና በተግባር በማሳየት ብቻ ነው፡፡

## 2.1.2 ደኢህዴን

ቀጥሎ ደኢህዴን እንዲሁ ባመዛኙ ወደ ትክክለኛ የተሃድሶ ጎዳና በመግባት ላይ ያለ ቢሆንም በውስጡ ጠንካራ አንድነት እና ቁጭት ገና አልፈጠረም በተለይ ጠባብነቱ ከፍተኛ ትግል የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፣ ስለዚ ወደኋላ የመመለስ ዓደጋም ተጋርጦበታል፣ ከዚህ ዓደጋ ለመላቀቅ በጣም ከፍተኛ ትንቅንቅ ያስፈልጓል፤

## 2.1.3 ብአዴን

ብአዴን ከገባበት የዝቅጠት ዓዘቅት ለመውጣት ወደ ተሃድሶ እንግባ አንግባ መወሰን አቅቶት ወደፊትም ወደኋላም እያለ በዝቅጠት አዙሪት ሆኖ ይዋዥቃል፡፡ ባለበት የዝቅጠት መንገድ ልቀጥል ወይስ ወደ ትክክለኛው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር ልመለስ የሚል ውሳኔ መወሰን አልቻለም፡፡ ብአዴን እንደ ህወሓት ረጅም የትግል ተሞክሮ ያለበት እና ከሌሎች /ከኦህዴድ እና ከደኢህዴን/ ቀድሞ የዝቅጠቱ አደጋ በመረዳት አብዮታዊ ዴሞክራሲ የማዳን ስራ ሊሰራ የሚገባው ድርጅት ነበር፡፡ ነገር ግን ችግሮችን ወደ ውስጥ ከማየት ይልቅ ምክንያቶችን መደርደር፣ ከህዝባዊነት ይልቅ ህዝበኝነት፣ ከአብዮታዊ ዝምድና ይልቅ ከመርሆ ውጭ ተራማጅ ያልሆነ ዝምድና

በማጠናከር አብዮታዊ ዴሞክራሲን አደጋላይ እንዲወድቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ ብአዴን የዝቅጠት መንገዱና ገደሉን ከርቀት እያየውና እየተገነዘበው ቢሆንም ወደ ኋላ የሚስበው የዝቅጠት ሃይል ሚዛን እየደፋ ነው፡፡ በአጠቃላይ ብአዴን ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይንም ከትምክህቱም ሳይሆን አጉል መሃል ላይ ተንሳፍፈዋል፡፡

ክቡር ጠ/ሚ ዶ/ር አብዪ አሕመድ በጎንደር እና በባህርዳር ባደረጉት ጉብኝት እና ከህዝብ ጋር ያደረጉት ውይይት ሲታይ መድረኮቹ ያንፀባረቁት ነገር ቢኖር ብአዴን በክልሉ ምን ያክል አብዮታዊ ዴሞክራሲን የማስረፅ ስራ እንደሰራና የዴሞክራሲያዊ አንድነት አመለካከት ያለበትን ደረጃ ያሳየ ነበር፡፡ መቸም ያልተዘራ አይታጨድምና በስብሰባዎቹ ሁሉም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አመለካከቶች ሳይሆኑ የትምክህት አስተሳሰቦች ጎልቶው የታዩባቸውና የተሃድሶ ድባብ ያልተንፀባረቀበት በመሆኑ ብአዴን እንደ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ሲታይ በከፍተኛ አደጋ ውስጥ እንዳለ ጎልቶ የታየባቸው መድረኮች ናቸው፡፡

## 2.1.4 ኦህዴድ

ኦህዴድ ከማንም በበለጠ መልኩ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አለኝታ መሆን ያለበት ድርጅት ነው፤ ነገር ግን ወደ ዝቅጠቱ እንደገባ የተመቸው ይመስላል፡፡ የመመለስ ዝንባሌም አይታይበትም፣ ይባስ ብሎ ትክክለኛ መንገድ ነው የያዝኩት በማለት የዝቅጠቱ ሻምፒዮን መሆን መርጧል፡፡ በጠቅላላ ከወዲያኛው ጎራ ግንባር ለመፍጠር መሯሯጥ ተያይዞታል፡፡ ሆኖም ግን ያኛው ጎራ እልም ያለ ገደል መሆኑ ባጭር ጊዜ ይገለጥለታል፣ ስለዚ ከእንቅልፉ መባነን የማይቀር ቢሆንም ከባድ ዋጋ ያስከፍለዋል፡፡

ከሁሉም የሚገርመው ኦሮሚያ ክልል ባለፉት ሁለት ዓመታት በአመፅና ነውጥ ሲታመስ ነበር የከረመው፡፡ በዚህ ወቅት ከፍተኛ የሃብትና የልማት አውታሮች ወድሟል፣ ዜጎች ማንነታቸው እንደ ወንጀል ተቆጥሮ ተፈናቅሏል፣ ተጎሳቁሏል፣ ህይወታቸው አልፏል፡፡ ይህ ጉዳይ ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ እስከ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መታወጅ ደርሷል፡፡ በአጠቃላይ የፌደራላዊና ህገመንግስታዊ ስርአታችን አደጋላይ አስገብቷል፡፡ በያዝነው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ስልጣን የሚያዘው ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እንደሆነ፣ መንገዱም ለሁሉም ክፍት መሆኑ እየታወቀ ወደ አመፅና ብጥብጥ መግባት አይጠበቅም፡፡ ነገር ግን ክቡር ጠ/ሚ ዶ/ር አብዪ አምቦ ባደረጉት ጉብኝት የተደረጉ ንግግሮች ሁሉም /የጠ/ሚ እንዲሁም የክልሉ ፕሬዚዳንት/ ያስተላለፉት መልእክት የጠ/ሚ ስልጣን የተገኘው በተደረገው ትግል ወይም የወጣቱ አመፅና ብጥብጥ ውጤት እንደሆነ፣ ለዚህም የተቀየሰ ስትራቴጂ እንደነበር እና የተቀየሰው ስትራቴጂም ውጤታማ እንደነበር በመግለፅ በአምቦ ህዝቡን የሰበሰቡት ምስጋናና ብስራት ለመግለፅ እንደ እንደሆነ ሁለቱም መሪዎች ገልፀዋል፡፡ ስለዚ ኦህዴድ የሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ

መንገድ ትቶ የአመፅና ነውጥ ስትራቴጂ እስከ መንደፍ የዘለቀ ዝቅጠት መግባቱ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፈፅሞ ተቀባይነት የለውም፡፡

### 2.1.5 አጠቃላይ እንደ ኢህአዴግ

በአጠቃላይ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች በግንባሩ ላይ የተደቀነውን አደጋ በመገንዘብ፣ ችግሮችን በማየት ከዚህ አስከፊ ችግር ለመውጣት እንደ ግንባር በፍፁም መግባባት ወደ ጥልቅ ተሃድሶ ለመግባት በመወሰን የተጀመረ እንቅስቃሴ ከሞላ ጎደል ሁለት ዓመት ያስቆጠረ ቢሆንም አመርቂ ውጤት አላመጣም ብቻ ሳይሆን፣ እንዲያውም በአባል ድርጅቶች መካከል የነበረው የመከፋፈል እና የአንድነት ችግር ሁሉም ሊገነዘበው በሚችል ሁኔታ ጎልቶ የወጣበት አደጋው አሳሳቢ ደረጃ መድረሱን አመላክቷል፡፡

በአጠቃላይ ኢህአዴግ ላለፉት 2-3 ዓመታት በግምገማና በጥልቅ ተሃድሶ ገብቶ ራሱን ለማጥራት የሚደረግ ትግልና ጥረት ቢኖርም፣ ከድርጅቱ የተሃድሶ ታሪክ አኳያ ሲታይ አበረታች አይደለም፡፡ እንዲያውም ኢህአዴግ እንደ ድርጅት በማይመጥነው የኪራይ ሰብሳቢነት አዘቅት ገብቶ በአዘቅቱ መዝለቅ አቅቶት ልክ መዋኘት የማይችል ሰው ወደ መዋኛ ስፍራ ገብቶ የህይወት ውጪ ህይወት ግቢ መፈራገጥ እንደሚታየው ሁሉ፣ ኢህአዴግም *በኪራይ ሰብሳቢነት ባህር ውስጥ ገብቶ መዋኘት አቅቶት እየተንፈራገጠ ያለ ድርጅት ነው* ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ኢህአዴግ ምን ያህል ወደ ዝቅጠት የገባ መሆኑ ለማሳያ ያክል አንዳንድ ነጥቦችን ለማንሳት እፈልጓሎ፡፡

## 2.2 የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መሸርሸር ምልክቶች

### 2.2.1 የቋንቋ ፖለቲካ

የኢህአዴግ እንደ ኢህአዴግ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር በመውጣት ላይ ያለ መሆኑ አንዱ ማሳያ በቋንቋ ላይ ያለ አተያይ ነው፡፡ ይህም ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ አመለካከት ውጭ ምክንያት እየደረደሩ የዓለም ተሞክሮ እየተጠቃቀሰ ለኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት 4-5 የስራ ቋንቋ ያስፈልጋታል፤ የሚሉ ጥያቄዎች ከልማትና ከድህነት ጥያቄ ቀድመው እየተስተናገዱ ይገኛሉ፡፡ ለዚህም ተገቢውን ትግል እየተደረገ አይደለም፡፡ ስለዚ አንዱ የመበስበስ ወይም ከመስመር የመውጣት ምልክት አድርጌ ወስጀዋለሁ፡፡ ማብራሪያውም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

#### ሀ. አማርኛ ለምን የአገራችን የስራ ቋንቋ ሆነ

አማርኛ የአገራችን ወይም የፌደራል የስራ ቋንቋ መሆን የቻለው በአገራችን የአማራ ህዝብ ከሌሎች የአገራችን ህዝቦች በርከት ያለ ቁጥር ስላለበት፣ ወይን ደግሞ የአማራ ተወላጆች በሁሉም ክልሎች በብዛት ስላሉ፣ ወይም የአማራ ተወላጆች ከሌላው ብሄር ብሄረሰብ መግባባት ስላልቻሉ ወይም ደግሞ ኢህዴን ወይም የአሁኑ ብአዴት

አማርኛ ቋንቋ የአገር የስራ ቋንቋ ለማድረግ ስለታገለ አይደለም፡፡ አማርኛ የስራ ቋንቋ የሆነበት ምክንያት ከአገራችን ቋንቋዎች በሁሉም ክልሎች የሚነገር ቋንቋ በመሆኑ፣ ላለፉት አንድ መቶ ዓመታትና ከዛ በላይ ጀምሮ በውድም በግድም በመላ አገሪቱ ብቸኛው ብሄራዊ ቋንቋ ሆኖ በማገልገሉ፣ በሁሉም የአገሪቷ አከባቢ ከመዋዕለ ህፃናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ካሪኩለም ተቀርፆለት በትምህርት ገበታ ላይ የቆየ በመሆኑ፤ በሁሉም የመንግስት መዋቅር፣ ከማእከላዊ መንግስት እስከ ቀበሌና ጎጥ የስራ ቋንቋ ኣማርኛ በመሆኑ፣ ላለፉት በርካታ አስርት ዓመታት ህዝቡ የመንግስት አገልግሎት ለማግኘይ የሚያደርገው መፃፃፍና ማንኛውም ዓይነት ግንኙነት በአማርኛ ይደረግ ስለነበር፣ በቀላሉ ሁሉም ክልሎች ለመግባቢያነት የሚመች ብቸኛው ቋንቋ በመሆኑና ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች ተማምነውበት በመወሰናቸው ነው፡፡ ስለዚህ አማርኛ የአገራችን የስራ ቋንቋ ሆኖ እንዲያገለግል መወሰኑ ትክክለኛ ውሳኔ ነበር፡፡

## ለ. የፌደራል የስራ ቋንቋ ጥያቄና ተገቢነቱ

በህዝቦች ይሁንታ የፀደቀውን ህገ-መንግስታችን እንደሚያሳየው በአገራችን ያሉ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በሙሉ እኩል እውቅናና እኩል መብት እንዳላቸው፣ አንዱ ከሌላው የማይበላለጡ እንደሆኑ በባህላቸው፣ በቋንቋቸው የመጠቀም፣ የማሳደግ እኩል መብት አጎናፅፏቸዋል፡፡ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብት ይከበራል ሲባል አንዱን ህዝብ ከሌላው ህዝብ አስበልጦ የሚታይበት አንዳች ነገር እንደሌለና ***10-ሺ ብዛት ያለውና 10-ሚሊዮን ብዛት ያለው ህዝብ ሁለቱም እኩል መብት፣ እኩል እውቅና አላቸው፡፡*** ሁለቱም በአገራዊ ጉዳይ በእኩል የመደመጥ መብት፣ የመወሰን መብት አላቸው፡፡ ይህ መብት ያረጋገጠ ህገመንግስት ያለን በመሆኑ ነው አገራችን ከመበታተን አፋፍ ያዳናት፡፡

ስለ ቋንቋ በምናይበት ጊዜ ***ሺ ተናጋሪ ያለውና ሚሊዮን ተናጋሪ ያለው ቋንቋ እኩል መብት እንዳላቸው በህገ-መንግስት ተረጋግጦዋል፡፡*** የዚህ ህገመንግስት ጠበቃ ናቸው የሚባሉ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ህገመንግስቱ በማክበር እና በማስከበር ረገድ ለወከሉትም ላልወከሉትም የአገራችን ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች አለኝታ እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ነገር ግን ለሁሉም ህዝቦች ብሄር ብሄረሰብና ህዝቦች መብት መከበር፣ ባህል ቋንቋ መከበር፣ እኩል በማየት ያከብራል ያስከብራል የተባሉ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የታጠቁትን መስመር መላላት በመጀመሩ፣ ቋንቋዎች ማበላለጥ ሲጀምሩ ምን ያክል ወደ ዝቅጠት መግባታቸው ያሳያል፡፡

ይህን በተጨባጭ ለማሳየት ያክል የኦህዴድ ስራአስፈፃሚ የአገራችን ቋንቋዎች በማበላለጥ፣ ህዝቦች በቁጥር በማስላትና በማበላለጥ የኔ ቋንቋ /ሌላው ቋንቋ የሱ እንዳልሆነ በመቁጠር/ የፌደራል የስራ ቋንቋ እንዲሆን እታገላለሁ ብሎ እርፍ፡፡ ከዚ የበለጠ የዝቅጠት ማስረጃ ምን ይምጣ፡፡ ***በአብዮታዊ ዴሞክራሲ እምነት ዙርያ የተደራጀ ድርጅት የህዝቦችን መብት በአጠቃላይ ያከብራል እንጂ ህዝቦችን እየለያየ የኔ ብሄር፣ የሌላ ብሄር እያለ***

***ወደ ዜሮ ድምር ጨዋታ አይገባም፡፡*** በዚህ ጉዳይ ብአዴንም ይህንን ሃሳብ በመጋራት ቋንቋዎች በማበላለጥ፣ ህዝቦች ከህዝቦች በማበላለጥ፣ ኦህዴድ ያለውን ትክክል ነው፣ እኛም ካሉት የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ህዝቦች የኦሮሚያ ክልል ስፋት ስላለው፣ ብዙ ህዝብ ስላለው፣ የኦሮምኛ ቋንቋ በክልላችን ትምህርት እንዲሰጥ እናደርጋለን በማለት የካሪኩለም ቀረፃ ጀምሯል፡፡

በእውነቱ እንነጋገር ከተባለ የኢትዮጵያ ህዝብ በአሁኑ ሰዓት ቀንደኛው ጥያቄ የቋንቋ ጥያቄ አይደለም፡፡ ዋናው ጥያቄ ልማት ነው፣ ዋናው ጥያቄ ድህነት ማጥፋት ነው፣ ያለውን በጣም ውሱን ሃብት እነዚህ ችግሮችን በመፍታት ስራ ላይ እንዲውልለት ይፈልጋል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ቀንደኛ ጠላቱ /ድህነት/ ለማጥፋት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ቋንቋ እንቅፋት ሆኖ በህዝቦች መካከል የተፈጠረ ያለመግባባት የለም፡፡

***የአማራ አርሶ አደር ያፈራውን ምርት ትግራይ፣ ዓፋር፣ ኦሮምያ ወይም ቤንሻንጉል ክልል ሂዶ እንዳይገበያይ ቋንቋ እንቅፋት ስለሆነብኝ የክልሉ መንግስት ይፍታልኝ ብሎ አልጠየቀም፣*** የጠየቀው ጥያቄ ኦሮሚያ ክልል ሂጄ የምገበያይበትን ***ምርት በእጥፍ ለማምረት መንግስት አቅም በመፍጠር፣ ቴክኖሎጂ አቅርብልኝ፣ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ ግብአት፣ ትምህርትና ስልጠና ይቅረብልኝ ነው ያለው፡፡***

የኦሮሞ ህዝብም አሁን ያለበትን አንገብጋቢ ጥያቄ በፌደራል መንግስት መስርያቤቶች ሂጀ በቋንቋ መግባባት ኣልቻልኩም፣ በክልሎች ሂጄ በቋንቋ ችግር መግባባት አልቻልኩም እና የቋንቋ ችግር መፍትሄ አስቀምጡልኝ ኣላለም፡፡ ***የኦሮሚያ ህዝብ አንገብጋቢ ጥያቄ ከማንኛውም የኢዮጵያ ህዝብ ጥያቄ ፈፅሞ የሚለይ ጥያቄ የለውም፡፡ ታድያ በዚህ ሰዓ የቋንቋ ጥያቄ ለምን ቀረበ ?*** ፀረ ህዝቦች የህዝቡን ጥያቄ አቅጣጫ ለማሳት የሚያደርጉት ሴራ ካልሆነ በስተቀር አሁንም የኦሮሚያ ክልል ህዝብ ቋንቋው ስላልተከበረለት ወይም የአገር የስራ ቋንቋ ስላልሆነ መብቴን አልተከበረልኝም አላለም፡፡ በሌሎች ወንድማማች ህዝቦች ቋንቋው እንዲጫንለትም አልጠየቀም፡፡

## ሐ. የቋንቋ ፖለቲካ መታረም አለበት

አሁን የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብት በተከበረበት፣ ተቻችሎና ተፈቃቅዶ መኖር በጀመረበት፣ ህገመንግስታዊ መብቶች ተከብረውለት ማጣጣም በጀመረበት ወቅት ይህንን የሚሸረሽርና በህዝቦች መካከል የታሪክ፣ የባህል፣ ልዩ አስተዋፅኦ፣ የህብ ብዛት ወዘተ የመሳሰሉ መስፈርቶችን በማምጣት ህዝቦች፣ ማንነቶች፣ ባህሎችና ቋንቋዎች ማበላለጥ ተገቢ አይደለም ከአንድ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የፖለቲካ ድርጅት /ከኦህዴድም ከብአዴንም/ የማይጠበቅ ድርጊት ነው፡፡ ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉንም ከ80 በላይ ቋንቋ መናገር ቢችል የሚጠላ የለም፡ ፡ ነገርግን ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንፃር ዋናው ችግር የቋንቋ ሳይሆን ድህነት ነው፣ ከፖለቲካ አንፃር ደግሞ በአሁኑ ሰዓት የተለያዩ ምክንያቶችን እየደደርክ የህዝቦችን መብቶች ማበላለጥ ከጥቅም ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል፡ ፡ ኢህአዴግ በዝቅጠት አደጋ ውስጥ ሆኖ፣ ከመበስበስ አደጋው ገና ሳይወጣ ይህ ጥያቄ የእንደዚህ ዓይነቱ

የህዝበኝነት ጥያቄ ማንሳት በጣም በጣም አደገኛ ነው፡፡ ይህ ጥያቄ የህዝባዊነት ምልክት ሳይሆን የመበስበስ የዝቅጠት ምልክት ነው፡፡ ዛሬ እንደዚህ አይነት የኔ ቋንቋ በሌሎች የመጫን ጥያቄ መጠየቅ፣ ነገ የአንድን ማንነት በሌሎች የብሄር ብሄረሰቦች በተደራቢነት ላይጠየቅ ወይም ላይጫን ምንም ዋስትና የለውም፡፡ ዋስትናችን አሁንም በጥልቅ ተሃድሶ በማለፍ አብዮታዊ ዴሞክራሲ አጥብቆ መያዝ ብቻ ነው፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ በኢትዮጵያ በድርጅት ይሁን በመንግስት ወይም በህግ የሚጫን ቋንቋ፣ ባህል፣ እምነት፣ ማንነት ፈፅሞ አይኖርም፡፡ በአሁኑ ወቅት ቻይና የዓለማችን ሁለተኛ ግዙፍ ኢኮኖሚ ባለቤት በመሆንዋ፣ የዓለማችን ህዝቦች ወይም አገራት የቻይና ቋንቋ በራሳቸው ጊዜ ፈልገው ለመማር ከፍተኛ መሯሯጥ ላይ ናቸው፣ ምክንያቱም ከቻይና ጋር ሆኖ መጠቀም ስለፈለጉ፡፡ በኛም ሁኔታ የኢትዮጵያ ህዝቦች በራሳቸው ጊዜ ፈልገውት ካልሆነ በስተቀር የህዝብ ብዛት ስላለ፣ ወይም ሌላ ምክንያት ስላለ በማለት ለሌላው አሳቢ በመምሰል ወይም በአውቅልህአለሁ የሚጫን ነገር አይኖርም፡ ፡ ስለዚህ ባፋጣኝ መታረምና ይቅርታ መጠየቅ አለበት፡፡ የተከበሩ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስተር ዶ/ር አብዪ አሕመድ ሁሉም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በአንድ አይን በማየት ያለምንም ልዩነት እንዲከበሩና እኩል እውቅና እንዲሰጣቸው ጥብቅና ይቆማሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡

## 2.2.2 የኢህአዴግ ሊቀመንበር ምርጫ

ሌላው የኢህአዴግ መበስበስ ጎልቶ የታየው በቅርቡ ኢህኣዴግ ምክርቤ ባደረገው ግምገማና የሊቀመንበሩ ምርጫ ላይ ነው፡፡ በዚህ ምርጫ ለተመልካችም ለሰሚም በሚገርም መልኩ ተፎካካሪ ፓርቲዎች፣ በውጭ የሚገኙ ተቋዋሚ ድርጅቶች በውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ሃይሎች ካላቸው አመለካከት በመነሳት የሊቀመንበርነት ምርጫው የየራሳቸው መላ ምት በመስጠት በጉጉት ሲጠብቁት የነበረ ነው፡፡ ይህ ምርጫም ጎራ ያደበላለቀና ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ እሴቶችና ከተራማጅነት ያፈነገጠ በመሆኑ እንዲሁም ጥልቅ ተሃድሶው የደረሰበትን ደረጃ በግልፅ ያሳየ በመሆኑ አንድ የትኩረት መስከ አድርጌዋለሁ፡፡ በዚህ የሊቀመንበርነት ምርጫ በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ውስጥ ሁለት ጫፎች የታዩበት ነበሩ፡፡ እነሱም

*በኢህአዴግም እንደ ግንባር እንዲሁም በየንዳንዱ አባል ድርጅቶች ያለውን የመበስበስ አደጋ እንዲሁም በችግሮቹ ጥልቀትና ስፋት ምን ያህል እንደሆነ፣ በህዝባችን ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ እንደሆነ፣ ህዝባችንን ይቅርታ መጠየቅ እንዳለብን የሚል ያለ ምንም ልዩነት መግባባት ላይ የተደረሰ ሲሆን የድርጅቱ ሊቀመንበር በመምረጥ ግን ሁለት ጫፎች ተስተውሏል፡፡ እነሱም* ***አንዱ ጫፍ*** *ህዝባችን ከልላችን በድለናል፣ የህዝቡ የልማት ጥማት፣ የመልካም አስተዳደር ፍላጎት ማርካት አልቻልንም፣ የሰማዕታት አደራ ረስተናል ስለዚህ ለህዝባችን ይቅርታ ጠይቀን ለመካስ ስለፈለግን የሊቀመንበርነቱን ምርጫ ይለፈን ሲሉ፤* ***ሌላው ጫፍ*** *ለህዝባችን ይቅርታ ጠይቀን ለመካስ ስለፈለግን የሊቀመንበርነቱን ዕድል ይሰጠን ለውጡን ማሳየት እንፈልጋለን ካልሆነ ሰላምና መረጋጋት በኢትዮጵያ*

*አይኖርም፡፡ የሚሉ ነበርይለፈን ሲሉ፡፡* ከዚህ በመነሳት የምርጫው ሂደት እና ውጤት ዴሞክራሲያዊነቱና ተራማጅነቱ ምን ይመስላል የሚል ከራሴ ትንታኔ በመነሳት ሳስቀምጠው እንደሚከተለው ይመስላል፡፡

የአንድ ተራማጅ ፖለቲካዊ ድርጅት ወይም ግንባር ዴሞክራሲያዊ ነው የሚያስብለው፣ ሓሳቦች ዴሞክራሲያዊና ነፃነት በተሞላው የሃሳብ ፍጭት በማድረግ ልዩነቶችን ማጥበብና ወደ መግባባት መድረስ፣ ካልተግባቡ በልዩነት በመለያየት የአብዛኛውን ድምፅ ይዞ ዴሞክራሲያዊ ትግል መቀጠል ነው፡፡ በምርጫ አካሄድም ቢሆን የአንድን ተመራጭ ያለውን ድክመትና ጥንካሬ ተዘርዝሮ የሚጨመር ወይም የሚስተካከል ካለም እንዲስተካከል ተደርጎ ወደ መግባባት ከተደረሰ ቦኋላ ወደ ምርጫ በመምጣት ድምፅ ይሰጥበታል፡፡ ድምፅ ከመሰጠቱ በፊት ግን ለድምፅ ማለፍ አለበት ወይም የለበትም የሚል የማረጋገጫ 1/3 ድጋፍ መኖሩ ከተረጋገጠ ቦኋላ ነው ወደ ድምፅ የሚታለፈው፡፡ በዴሞክራሲያዊ አሰራር ዋናውና ወሳኝ ነገር፣ በምርጫም ይሁን በውሳኔ አሰጣጥ የመጨረሻው ውጤት ብቻ ሳይሆን ወደ ውጤቱ ለመምጣት የተደረገው ውይይት እና ትግል ሂደት ነው፡፡ ይህ ውይይትና ትግል ደግሞ ተራማጅና ዴሞክራሲያዊ ነበር የሚያስብለው፣ የመጨረሻው ውጤት ወይም ውሳኔና ምርጫ በመድረኩ ውስጥ በተደረጉት ውይይቶችና ትግሎች ብቻ ተወስኖ የተገኘ ውጤት ሲሆን ነው፡፡ ከዚህ ውይይትና ትግል ውጭ የሚደረግ ወይም የሚመጣ የምርጫ ውጤት ፍፁም ዴሞክራሲያዊ የሚያስብሉ መስፈርቶች በሟሟላት ቢፈፀምም ተራማጅ ኣያስብልም፡፡ በተራማጅ ድርጅት ውስጥ ወይም በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ድርጅት ውስጥ የዴሞክራሲያዊነት መገለጫ ነፃነት በተሞላው ድምፅ እንዲሰጥ በማድረግ የአብዛኛው ድምፅ ውሳኔ ተቀብሎ መሄድ ብቻ የታጠረ አይደለም፡፡ ዴሞክራሲያዊና ተራማጅ የሚያስብለው ምርጫው ፍፁም ነፃና ዴሞክራሲያዊ ሲሆንና የምርጫው ውጤትም የዴሞክራሲያዊ ትግሉን የሚያንፀባርቅ ከሆነ ነው፡፡ በዴሞክራሲያዊና ሕጋዊ መድረክ በተደረጉ ውይይቶችና ግምገማዎች መግባባት ተደርሶ ነገርግን በምርጫው ላይ ከፍተኛ ልዩነት ከተንፀባረቀ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ቢሆንም ተራማጅ ሊሆን ግን አይችልም፡፡

ለምሳሌ አንድን በጎሳ ወይም በባህላዊና ልማዳዊ የዘር-ሃረግ ስርዓት የሚተዳደር ህብረተሰብ ባለበት አከባቢ መሪ መምጣት ያለበት በዘር ሃረግ ነው የሚል ጠንካራ እምነት ያለበት ከሆነ፣ ይህ እምነቱ በዴሞክራሲያዊ እምነት ካልተተካ በስተቀር የፈለገው ዴሞክራሲያዊ ትግል ቢደረግም ውጤቱ ዴሞክራሲያዊ ውጤት ሊሆን አይችልም፡ ፡ ምክንያቱም የፈለገው ትግል ቢደረግም በህዝቡ ውስጥ ያለውን ባህላዊ እምነት ሚዛን ስለሚወስድ የመድረኩ ወይም የትግሉ ውጤት ሳይሆን አሸናፊ የሚሆነው የባህላዊው እምነት ነው አሸናፊ የሚሆነው፡፡ ስለዚ ነፃ ድምፅ አሰጣጥ ስለተደረገ ብቻ ዴሞክራሲያዊ አያስብለውም፡፡

አሁን በኢህአዴግ የተደረገው ምርጫ በዝርዝር ግምገማና ትግል ላይ የተደረሰ እንደሆነ የግንባሩ ስራአስፈፃሚ መግለጫ አትተዋል፡፡ በዝርዝር ግምገማው ላይም ሰፊ መግባባት እንደተደረሰ ያስረዳል፡፡ በተለይ ዳግም ጥልቅ ተሃድሶ ላይ የተለዩ ችግሮችን በዝርዝር ቀርበው ልባዊ በሆነ መንገድ ሁሉንም እንደተቀበለውና የድርጅቱ ችግር

እንደሆነ መተማመን ላይ እንደተደረሰ ተገልፀዋል፡፡ እንደ መግለጫው ቢሆን ጥሩ ነበር ነገር ግን የምርጫው ውጤት በምናይበት ጊዜ ግምገማውና ውጤቱ ለየብቻ ናቸው፡፡ ምክንያቱም በግምገማላይ በትክክል መግባባት ላይ ከተደረሰ ውጤቱም የዚህ ማሳያ መሆን ነበረበት፣ ነገር ግን የምርጫው ውጤት የመግባባት ምልክት ሳይሆን የከፍተኛ ልዩነት ምልክት የተንፀባረቀበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ምክንያቱም ለግንባሩ ሊቀመንበር ነት ከፍተኛው ድምፅ የተገኘው ከጠቅላላው የምክርቤት አባል 108 ብቻ ሲሆን ይህም ከተገኙት ኣባላት ውስጥ 64% ሲሆን ከጠቅላላው የምክርቤት ኣባላት ደግሞ 60% ማለት ነው ስለዚ ከ38-40% የሚደርስ ተቋውሞ ኣለ ማለት ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም፡፡ በኢህአዴግ የትግል ታሪክ ውስጥ ያየነውና የተማርነው ነገር ቢኖር በሚደረጉ ተራማጅና ዴሞክራሲያዊና የውሳኔ ይሁን የምርጫ ውጤቶች ከ97% በላይ ነበሩ፣ የተቀሩት ከ3% በታች ግን መጠነኛ ልዩነቶችና በአመዛኙ ስህተቶች (Errors) ነበር፡፡ ውጤቱ 50%+1 እስከ ሆነ ድረስ በድርጅት አሰራርም በደሞክራሲያዊ ስርዓትም ተቀባይነት ያለውና ዴሞክራሲያዊ ነው ቢባልም፡፡ ከድርጅት ታሪክ፣ ከተራማጅነትና ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ እሴቶችና መርሆዎች አንፃር ሲታይ ግን ኢህአዴግ እስካሁን ካካሄዳቸው ምርጫዎችና ዴሞክራሲያዊ ውሳኔዎች አንፃር ሲታይ የወረደ እና ደረጃውን ያልጠበቀ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ይህ ምርጫ ኢህአዴግ በታሩኩ መሪውን በመምረጥ ረገድ ከፍተኛ ልዩነት የተመዘገበበት የመሪ ምርጫ ተብሎ የሚወሰድ ነው፡፡ አንድዓይነት ዓላማ ይዞ፣ አንድ አይነት መስመር /አብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም ልማታዊ ዴሞክራሲ/ ይዞ አንድ አይነት መርሆና እሴት ይዞ ፣ የአሜሪካው ዲሞክራትና ሪፓብሊካን ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ እስኪ መስል ድረስ እንዲህ አይነት ውሳኔ መስጠት በጣም በጣም ችግር ላይ እንዳለ ያሳያል፡፡ 36% ማለት ከአንድ ድርጅት በላይ ማለት ነው ይቅርና እንደዚህ አይነት ከፍተኛ ልዩነት ሊኖር የግለሰቦች ልዩነት ሲያጋጥምም አስቸጋሪ ነው፡፡

የችግሩ አሳሳቢነት ከፍተኛ የሚያደርገው ደግሞ በዳግም ጥልቅ ተሃድሶ ማግስት መሆኑ፡፡ ከአሁን በፊት ኢህአዴግ 2 ስር-ነቀል ተሃድሶዎች አድርጎ ሲያበቃ በአመራረና በአባሉ ብሎም በህዝቡ ጠንካራ አንድነት ፈጥሮ ልባዊ መተማመን ፈጥሮ ነበር ወደ ትግልና ወደ መስዋእትነት ሜዳው የሚሄድ የነበረው፡፡ የዛሬው ምርጫ ግን በጣም የሚገርመው ምርጫው ከመካሄዱ በፊት በውጭ ተጨርሶ የመጣ ነበር የሚመስለው፡፡ ምክንያቱ የተከበሩ የኢህአዴግ ምክትል ሊቀመንበር አቶ ደመቀ መኮንን በሚድያ ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጡ እንደጠቀሱት

***መጀመሪያ በግለሴ አዲስ ፊት እንዲመጣ እፈልግ ነበር፣ ይህን ፍላጎታ ከብአዴን አመራር መከርኩበት የሚቃወሙ ቢኖሮም ግን መግባባት ላይ ደረስን፣ ቀጥለ ከሌሎች አመራሮች /እኔ እንደገባኝ ከአህደዴድ አመራር ይመስለኛል/ ተነጋገርንበት ተግባባን በመጨረሻም ያሰብኩት ወይም የፈለኩት ውጤት መጣ በማለት መግለጫ ሰጥቷል፡፡***

የተከበሩ አቶ ደመቀ መኮንን በሰጡት መግለጫ ሁለት ጥያቄዎች ያስነሳል፡-

1. በእውነት አዲስ ፊት ከተፈለገ ክቡር ምክትል ሊቀመንበሩ በብአዴን የዳግም ተሃድሶ መድረክ አቅርበው ለምን አልተገበሩትም ወይም በብአዴን አዲስ ፊት አላስፈለገም ለማለት ይሆን?
2. በኢህአዴግ አሰራርና ስነስርዓት ከምርጫው በፊት እኔን አትምረጡ እከሌን /አዲስ ፊት/ ምረጡ ተባብሎ መነጋገርና የምርጫ ቅስቀሳ ይደረጋል እንዴ ? መርሆ ያልተከተለ ግንኙነት በድርጅቶች ማኸል አለ ሲባል ትክክለኛው መገለጫ ከዚህ ውጭ ሊሆን አይችልም፡፡

### 2.2.3 የኪራይ ሰብሳቢነትን መታገል ያቃተው አመራር

ኢህአዴግ በአፍሪካ በዘመናዊ ትጥቁና በሰራዊት ብዛት ተወዳዳሪ ያልነበረው የደርግን ስርዓት በአጭር ጊዜ /በ17 የትጥቅ ትግል/ የገረሰሰና፣ ወርቅ የሆነ ሁሉንም የሚያማልል ፕሮግራም ያለው ድርጅት ሆኖ ሳለ፣ ልማት በአገሪቱ እንዲሳለጥና የአገራችን ገፅታ በዓለም አቀፍ አደባባይ እንዲለወጥ እንዲሁም አገራችን በአፍሪካ የኢንቨስትመንት መዳረሻ እንድትሆን ያደረገው አንጋፋ ድርጅት ሆኖ ሳለ፣ የውስጡን መዥገሮች ማስታገስና ከመሰረታቸው መንቀል ባለመቻሉ የህዝቡ እርካታ ወደ ዝቅተኛ ደረጃ እንዲወርድ ሆኖዋል፡፡ እርካታ ወደ ዝቅተኛ ደረጃ መውረድ ብቻ ሳይሆን በዚህ ችግር ምክንያት የተነሳ ህዝቡ በስርዓቱ የሚደርሱትን አደጋ በወኔና በባለቤትነት ስሜት ለመመከት ዳተኝነት እየተሰማው ነው፡፡ በውስጥ የአመራር ድክመቶች፣ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እሴቶችና መርሆዎች መሸርሸር ችግሮች፣ የመልካም አስተዳደር እና የኪራይ ሰብሳቢነት ችግሮች፤ በውጭ የፀረሰላምና የፀረ ህዝብ ሃይሎች አፍራሽ ፕሮፖጋንዳ ተደማምረው በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ ጥርጣሬ እንዲኖረው አድርጓል፡፡ ይህ ጉዳይ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ቢወቀጥ፣ ቢዎቀጥ እምቦች ሆኖ ቀርቷል፤ ስለዚህ ይህንን ነቀርሳ መንግሎ የሚያወጣ ቆራጥ አመራር ትፈልጋለች አገራችን፡፡ ይህ ጉዳይ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ህልውና የሚወስን ጉዳይ በመሆኑ ህዝቡ በጉጉት የሚጠብቀው ነገር ነው፡፡ በዚህ ሰዓት አገራችን የምትፈልገው አመራር /ኬትም ይምጣ ኬትም/ ህዝቡ በጉጉት እየጠበቀ ያለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም ልማታዊ ዴሞክራሲ መስመር እና እሴቶችን አጥብቆ የሚይዝ ነው፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ ግን በአሁኑ ሰዓት ኢህአዴግ ከመቸውም በበለጠ ከመበስበስና ከዝቅጠት አዘቅት የሚያወጣው የውስጥ ሓይል ይፈልጋል፡፡ የኢህአዴግ ኣባል ድርጅቶች በአሁኑ ደረጃ አፍን ሞልቶ ታድሷል ለማለት አያስደፍርም፡፡ በተለይ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስተር ክቡር ዶ/ር አብዪ የሚመሩት ድርጅት ጨምሮ ሌሎች የኢህአዴግ ኣባል ድርጅቶችም ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ እሴቶችና መርሆዎች ውጭ ሲንቀሳቀሱና በዝቅጠ አዘቅት

ተዘፍቆ የለውጡ/የተሃድሶው ሻምፒዮን መስሎ ለመታየት በመሞከር፣ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲና ከተራማጅ አስተሳሰብ በመውጣት፣ ቀላል የማይባል ርቀት ተጉዟል በመጓዝም ላይ ናቸው፡፡

### 2.2.4 የጎራ መደበላለቅ

- #### አብሮ የመስራት ጥሪ

አገራችን ኢትዮጵያ ሁሉም ህዝቦችዋ የተሳተፉበት ዘመናዊና ዴሞክራሲያዊ ህገመንግስት በማፀደቅ ተግባራዊ ከማድረግ ኣኳያ እነሆ 23 ዓመታት አስቆጥሮዋል፡፡ በዚህ የህገመንግስት ዘመን 5 ተከታታይ ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ነፃና በህዝብ ዘንድ ተአማኒነት ያተረፈ የህዝብ ምርጫ ተካሂዷል፡፡ የዴሞክራሲ ምህዳሩ ለማስፋት በተደረገው ጥረት አበረታች ውጤት የተመዘገበ ሲሆን እስከ 75 የሚደርሱ በህጋዊ መንገድ ለመንቀሳቀስ የተመዘገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተፈጥረው በመንቀሳቀስ ላይ የነበሩ ሲሆን፣ የሚከስሙ እየከሰሙ፣ ገሚሶቹ ጥምረትና ቅንጅት እየፈጠሩ፣ ኣዳዲሶችም እየተመሰረቱ እስከ አሁን ድረስ ጠቅላላ ወደ 65 የሚሆነየ ተቃዋሚ/ተፎካካሪ ድርጅቶች አሉ፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ የትግል ሜዳ ረግጠው፣ በግብፅና በሻዕብያ እየተደገፉ ህገመንግስታዊ ስርዓት በሃይል ለማፍረስ በማለም በውጭም በአገር ውስጥም የሚንቀሳቀሱ ፀረ-ህዝብና ፀረ-ዴሞክራሲ ሓይሎች ኣሉ፡፡ እነዚህ ሃይሎች ካላቸው ባህሪና እንቅስቃሴ በመነሳት በሀአገራችን ፓርላማ በአሸባሪነት የፈረጃቸውን ድርጅቶች ኣሉ፡፡ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ከነዚህ አሸባሪዎች እርቅ ለመፈፀም የሰላም ጥሪ ማድረጉ ምን ይባላል? ላለፉት 17 ዓመታት የአገራችን የተሃድሶ እንቅስቃሴ ለመቀልበስ፣ በተደራጀም በግልም ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ የነበሩ የቀድሞ የኢህአዴግ አመራሮችን እርቅ ፈፅሞ በህዝብ/ድርጅት ገንዘብ ድጎማዎች ማድረጉ በአደባባይ ያለሀፍረት ሲገለፅ ማየት፣ ከአቋም መሸርሸር ሌላ ምን ትርጉም ሊሰጠው ይችላል?

- #### በባንዲራዎቻችን ያለን እምነት መሸርሸር

በአገራችን ያለው የፖለቲካ አሰላለፍ በሁለት ይከፈላል፣ እሱም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ (ልማታዊ ዴሞክራሲ) አሰላለፍ እና የኪራይ ሰብሳቢነት (ባላደጉ አገሮች ውስጥ ያለ ሊበራል) አሰላለፍ ማለት ይቻላል፡፡ የነዚህ ሁለት አሰላለፎች አንዱና ዋነኛው ልዩነታቸው በዴሞክራሲ ያለ አመለካከት ነው፡፡ እሱም በቡድን መብት አከባበር ላይ ነው፡፡ የሊበራል አሰላለፎች የግል መብት እውቅና በመስጠት እና ከለላ በማድረግ ሁሉም መብቶች ይከበራሉ ስለዚ የቡድን መብት የሚባል የለም ሲል፤ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አሰላለፍ ደግሞ ሁለቱም የማይነጣጠሉና የማይተካኩ በመሆናቸው የሁለቱም መብት መከበር እና ከለላ መስጠት ያስፈልጋል በማለት ሲከራከር የዚህ

መገለጫም በአገራችን ያሉ ብሄር ብሄረሰቦች ሙሉ መብት መከበር አለባቸው በማለት ባለፉት 27 ዓመታት ሰፊ ስራ ተሰርቶዋል፡፡ የዚህ መብት መከበር ማሳያው እንደ ብዙሃነታችን የማንነታችን መገለጫ የሆኑ የተለያዩ ህብረ ቀለም ያላቸው ባንዲራዎቻችንና ሲሆን የአብሮነታችንና የእኩልነታችን መግለጫ ደግሞ አረንጓዴ ብጫ ቀይ ላይ የብዙሃነታችን ማሳያ የሆነ የኮከብ አርማ ያለበት ሰንደቃችን ነው፡፡ እነዚህ ባንዲራዎቻችንና የማንነታችን አርማዎች በደስታችን፣ በሃዘናችን፣ በማንኛውም ህዝባዊና ማህበራዊ ግንኙነቶችና ስብሰባዎች አደባባይ ላይ ይወጣሉ፡፡ በትላልቅ መድረኮች እነዚህ ባንዴራዎች መውጣት ማለት በአገራችን ያሉ ብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት መገለጫ ነው፡፡ አሁን እየታዘብነው ያለ ነገር ግን በጣም በሚገርም ሁኔታ እነዚህ ባንዴራ አደባባይ እንዳይወጡ የታዘዙ ይመስል ስብሰባዎቻችን በተለይ የአዲሱ ጠ/ሚ የሚጠርዋቸው ስብሰባዎች እነዚህ ባንዴራ አደባባይ አልወጡም፡፡ ለምን?

በርግጥ ነው ባለፉት 27 ዓመታት በመርህ ደረጃ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በአንድነት ላይ የማያወላዳ አቋም ያለው ሲሆን ከትምክህቱ ጎራ የሚለየው፤ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ለኢትዮጵያ አንድነት መከበር የብሄር ብሄረሰቦች መብት እንደ ቅድመ ሁኔታ ሲያስቀምጥ፣ የትምክህቱ ጎራ ደግሞ የኢትዮጵያ አንድነት ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ይላል፡ ፡ መሰረታዊ ልዩነቱ ይህ ነው፡፡ የትምክህቱ አስተሳሰብ በአገራችን ለ100 ዓመታት የመንግስት አስተሳሰብ ሆኖ በመቆየቱ አገራችን ወደ መበታተን አፋፍ አድርሶ የነበረ ሲሆን፣ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ግን ባለፉት 27 ዓመታት ትምክህት የፈጠረው ቁስል በማከም በምትኩ በእኩልነት፣ በመቻቻል፣ እና በመፈቃቀር ላይ የተመሰረተ ጠንካራ መሰረት በማበጀት ላይ ነው፡፡ ይሁንና ጠ/ሚንስትሩ እንደገለፁት አብዮታዊ ዴሞክራሲ በፕሮፖጋንዳው ትኩረት የሰጠው ተረስቶ ለነበረ የማንነይና የብዙሃነት መብት ነበር፣ በዛ ልክ ለአንድነት በፕረፖጋንዳ ቅስቀሳ ደረጃ አልተሰራም፡፡ ስለዚ አሁን ይህን ክፍተት መሙላት አለብን ሲባል ችግር የለውም፣ እንዲያውም አብዮታዊ ዴሞክራሲ በበለጠ ስር እንዲሰድ ያደርግ እንደሆነ እንጂ፡፡

ችግር የሚሆነው አሁንም የተረሳውን ብቻ ትኩረት በመስጠት የብዙሃነትና የማንነት መገለጫችን ሙብቶች ችላ ማለት ከመጣ ነው፡፡ ኢህአዴግ ይታገልለት የነበረውን የብዙሃን መብትና የብሄር ብሄረሰቦች መብት በአንድነት ስም ችላ ማለትና በሱ ፋንታ አንድነትን መተካት ከመጣ አብዮታዊ ዴሞክራሲ አደጋላይ ወደቀ ማለት ነው፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ያስገኘልንን ድል በመጠበቅ ተጨማሪ በአንድነት ዙርያ መስራት በትክክል ያስፈልጋል፡፡ የክልሎች የማንነት አርማቸው ጣል ጣል ማድረግ ግን ያቀያይመናል፡፡ አሁን አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስተር ከተመረጠ በኋላ ባለፉት ጥቂት ቀናት የታዘብነው ነገር

1. ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከመላ አገሪቱ ለተጋበዙ 25000 የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ተወካዮች በተገኙበት በሚሊኒየም አዳራሽ ደማቅ ስነስርዓት የተደረገ ሲሆን፣ የአዳራሹ መዋብ ሲታይ አንድ ትልቅ

ነገር የጎደለው ሆኖ ታየኝ እሱም የውበታችን መለያ፣ የዴሞክራሲያዊ አንድነታችን ማሳያ የሆኑት የየብሄር ብሄረሰቦች መለያ ባንዴራ አንድም አልነበረም፡፡ ታድያ እነዚህ የውበታችን ምልክትና የብዙሃነታችን ማሳያ ህብረ ቀለሞቻችን ለምን ቀሩ? የአገራችን አረንጓዴ ብጫ ቀይ ባንዲራ ከነ ሙሉ /ኮከብ/ አርማው የብዙሃነታችን ማሳያ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም የያንዳንዱ ክልል የማንነት ባንዴራ ለምን ተተወ? ያሳፍራል እንዴ? ትምክህተኞችን ለማስደደሰት ነው? ወይስ እርቅ ፈልገናል?





የመጀመሪያው ስዕል የሚሊንየም አዳራሽ ሆኖ ከአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስተር ዶ/ር አብዪ መመረጥ በፊት ሲሆን ቀጥሎ ያለው ደግሞ በተመሳሳይ አዳራሽ አዲሱ ጠ/ሚ ከተመረጡ ቦኋላ የተደረገ ስብሰባ ሆኖ የመጀመሪያው በክልሎችና በፌደራል ባንዲራ ሲዋብ ሁለተኛው ግን በፌደራል ባንዲራ ብቻ፡፡

2. አሁንም ክቡር ጠ/ሚ ዶ/ር አብዪ አሕመድ አማራ ክልል በጎበኙበት ወቅት በተመሳሳይ መልኩ በስብሰባው አዳራሕ የክልሉ ባንዴራ (የካሜራ ማን ችግር ይሆን?) ፈልጌ አጣሁ፤ በተጨማሪም ጥያቄዎቹ ያለ አንዳች ህፍረት እልም ያሉ የትምክህት አመለካከት የተጠናወታቸው ወገኖች መድረኩን የተቆጣጠሩት ይመስል ነበር፡፡ ክልሉ ባንዴራውን ራሱ ካላከበረው ማን ሊያከብርለት ይጠብቃል?





የመጀመሪያው ስዕል መቐለ ሲሆን ተሳታፊው የክልሉ እና የፌደራል ባንዴራ ሲያውለበልብ ኣዳራሹም በሁለቱም ባንዲራዎች አሸብርቋል፡፡ ቀጥሎ ያለው ስዕል በጥቂት ቀናት ልዩነት ባህርዳር ላይ ሆኖ አንድም የክልሉ ባንዲራ የለም በፌደራል ባንዲራ ብቻ ተውበዋል፡፡

3. የነዚህ መፅናኛ ግን በሶማሌ፣ በኦሮሚያ እና በትግራይ የታዘብነው የክልላቸው ባንዲራ ተገቢውን ክብር በመስጠት የአብሮነታችንና የአንድነታችን ባንዲራ አብሮ ተገቢውን ቦታ ተሰጥቶ በመቀመጣቸው አድናቆቴን መግለፅ እወዳለሁ፡፡





ስለዚ አሁን በ21ኛው ክፍለዘመን ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የሚያስብላት፣ አንድነቷ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሚያደርጋት፣ የብሄር ብሄረሰቦች እና የብዙሃነት እውቅና በመስጠትና ተገቢውን ክብር በመስጠት ብቻና ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የተከበሩ ጠ/ሚ ዶ/ር አብዪ ለዚህ ጉዳይ እስከ ሂይወት መስዋእትነት ለመክፈል በለጋ እድሜዎ ብረት ማንሳትዎና በመጨረሻም ለድል መብቃትዎ ለሁሉም ግልፅ ነው፣ ስለዚ ለወጡለት ዓላማና ከሰማእታት ለተቀበሉት አደራ ፀንተው በመቆም ተገቢውን ክብር እንዲሰጡልን በታላቅ አክብሮት መጠየቅ እወዳለሁ፡፡

## • እስረኞችን በመፍታት ላይ የተንፀባረቀው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መሸርሸር

ሁሉም የሚያውቀው ህገመንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለማፍረስ የሞከሩ ሃይሎች በሰሩት የወንጀል ድርጊት መታሰራቸውን ይታወቃል፡፡ አሁን ባለንበት ስርዓት በኢትዮጵያ ብሄራዊ ማንነቱ እንደ ወንጀል ተቆጥሮ አንድም ሰው የታሰረ እንደሌለ ሁሉም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ያውቃሉ፡፡ ካለም ከእስር ወጥቶ እሱን ያስገባ ኣካል እስርቤቱ መግባት አለበት፡፡ ነገርግን በኔ እምነትም ብሄራዊ ማንነት እንደ ወንጀል ተቆጥሮ የታሰረ ሰው የለም፡ ፡ ነገር ግን የዝቅጠቱ ደረጃ ምን ያክል እንደወረደ የሚያሳየው፤ እየታሰረ ያለው የተወሰነ ብሄር አባል ነው፣ ስለዚ መፈታት አለበት ተብሎ ወንጀለኞች፣ ብዙ የፀጥታ ሃይሎችን የገደሉ ሳይቀር ሲለቀቁ ያሳዝናል፡፡ እነዚህ የተለቀቁ ሰዎች ባላጠፉት ወንጀል፣ ለህገመንግስታዊ ስርዓቱ አደጋ ሳይሆኑ እንደ አደጋ ተደርጎ ከሆነ የታሰሩ፤ በምትካቸው ይህን የፈፀመ ባለስልጣን ሊገባ ይገባዋል እንጂ በስመ ይቅርታ መታለፍ ያለበት አይደለም፡፡ ነገር ግን እውነታው

እንደሱ አይደለም፡፡ እውነታው በኢህአዴግ አመራር ውስጥ የጎራ መደበላለቅ መፈጠሩ ነው፡፡ የብሄር ማመጣጠን ይመስል በእስርቤት ያለውን እስረኛ ብሄራዊ ማንነቱ በመቁጠር የማመጣጠን ስራ መስራት እውነትም የጎራ መደበላለቅ ያስብላል፡፡

- ## በፓርላማ ውሳኔ አሰጣጥ የፀረ ሰላም አቋም መያዝ

በአመራር ችግር ምክንያት ላለፉት ሁለት ዓመታት አገራችን ከፍተኛ አደጋ ተጋርጦባት በአመፅና ነውጥ ስትናጥ ከርማለች፡፡ በዚህ ጊዜ የአስቸካይጊዜ ታውጆ ለማረጋጋት ተሞክሮ መጠነኛ ውጤት የተገኘ ቢሆንም መሰረታዊ ለውጥ ግን አልተረጋገጠም፡፡ በመሆኑም ነውጡና አመፁ ዳግም አገርሽቶ የዜጎች መፈናቀል፣ የሃብትና ንብረት መቃጠልና መውደም፣ የልማት አውታሮች መውደምና መዝረፍ፣ የትራንስፖርት አውታሮች መዝጋት፣ የንግድና የገበያ ቦታዎች መዝጋትና ማስተጓጎል በአጠቃላይ የዜጎች ህገመንግስታዊ መብቶች በሙሉ እየተጣሱ ሃይ ባይ ታጥቶ በህዝቦች መካከል ጥርጣሬና ስጋት ተንሰራፍቶ በአጠቃላይ በህገመንግስታዊ ስርዓታችን ትልቅ አደጋ መደቀኑ ነጋሪ የማያስፈልገው ሁሉንም የሚያውቀውና የሚያየው ጉዳይ ሁኖ ነበር፡፡ የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያለውን ሁኔታ በመገምገም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መታወጅ አለበት ብሎ በመወሰኑ፣ የህዝብ ተወኳዮች ምክርቤት ተሰብስቦ እስኪያፀድቀው ድረስ፣ ህገመንግስቱ በሚፈቅደው መሰረት ለሁለት ሳምታት በሚኒስትሮች ምክርቤት ተቀባይነት አግኝቶ መታወቁ ይታወቃል፡፡ ይህን አዋጅ ለማስቀጠል በፓርላማ አጀንዳ ተከፍቶ ለውሳኔ በቀረበበት ጊዜ፣ ኢህአዴግና አጋሮቹ በሚቆጣጠሩት ፓርላማ በአብላጫ ድምፅ ሲፀድቅ የድምፁ ሁኔታ ሲታይ ግን በጣም አሳፋሪ ነበር፡፡ አሳፋሪ የሚያደርገው ነገር በአገር ላይ የተደቀነ አደጋ ሁሉም እየሰማውና እያየው፣ ግማሹም በችግሩ እየተሰቃየ፣ ሰላምና መረጋጋት ርቀው ህዝቡ እያማረረ ባለበት ሁኔታ፣ የኦሮምያ ክልል መስተዳድር ይህን ማረጋጋት አቅቶት እየተባባሰ እየሄደ፣ ብሎም እየተባባሰ ወደ ሌሎች አጎራባቾች እየሄደና አገር አደጋውስጥ ገብታ እያለ፤ በህዝብ ተወካዮች ምክርቤት አብዛኛው የኦህዴድ የፓርላማ አባል /ከ52% በላይ/ የኦነግና የጀዋር አሕመድ የፀረሰላምና የፀረህዝብ ጥሪ ተቀብሎ መቆሙ ነበር፡፡

በማንኛውም የዴሞክራሲና የተራማጅነት አስተሳሰብ መለኪያ፣ አንድን የድርጅት ውክልና ይዞ ፓርላማ የገባ ተወካይ የድርጅቱን ውሳኔ ጥሶ ድምፅ መስጠት አይችልም፡፡ ያየነው ነገር ግን ይህ ነው፡፡ ታድያ ከዚ የበለጠ የዝቅጠትና የመበስበስ መገለጫ ምን አለ፡፡ አንድን አብዮታዊ ዴሞክራሲ እምነት ይዞ የሚመራ ድርጅት የፀረ ሰላም አቋም፣ የፀረ ህዝብ አቋም ደግፎ ያለሀፍረት ሲቆም በጣም ያስገርማል፡፡

# 3 የአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስተር ብቃትና ተቀባይነት

የቀድሞ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስተር እና የደኢህዴን ሊቀመንበር ክቡር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የስልጣን መልቀቂያ ጥያቄ ካቀረቡ ቦኋላ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የኢህአዴግ ምክርቤት ተሰብስቦ የጎደለውን የአመራር

ቦታ /የግንባሩ ሊቀመንበር/ ለመሙላት ታሪካዊ ምርጫ አካሂዷል፡፡ በዚህ ምርጫ የኦህዴድ ሊቀመንበር የሆኑት ክቡር ዶ/ር አብዪ አሕመድ የኢህአዴግ ሊቀመንበር አድርጎ በአብላጫ ድምፅ መርጧቸዋል፡፡ በአገራችን ሕገመንግስት መሰረት በህዝብ ምርጫ ኣብላጫ ድምፅ ያገኘ የፖለቲካ ድርጅት መንግስት የሚመሰርት ሲሆን የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስተርም መርጦ ይሰይማል፡፡ በዚህ መሰረት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስተር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የስልጣን መልቀቂያ ካቀረቡ ቦኋላ የኢህአዴግ ለግንባሩ በሊቀመንበርነት የመረጣቸውን የተከበሩ ዶ/ር አብዪ አሕመድ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ በጠቅላይ ሚኒስተርነት እንዲሰየሙ ማድረጉ ህጉን የተከተለ እና ተቀባይነት ያለው በመሆኑ ሁሉም ከጎናቸው መሰለፍ አለበት፡፡

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስተር ዶ/ር አብዪ አሕመድ በጠቅላይ ሚኒስተርነት ከተሾሙ ቦኋላ በተለያዩ ክልሎች ከህዝብ ጋር የሚተዋወቁበት መድረኮችን በማዘጋጀት ውጤታማ ሊባል የሚችሉ ውይይት በማካሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡ በተለይ በተወካዮች ምክርቤት ያደረጉት ንግግር የብዙ ሰው ቀልብ የሳቡ ሲሆን ከህዝቡ ጋር ፊት ለፊት ያደረጉት ንግግርና በመድረኮችን ለተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ማብራርያ ሲሰጡ ከፍተኛ ተቀባይነት በማግኘት ላይ ናቸው፡፡ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስተር በለጋ ዕድሜያቸው ጀምሮ ወደ ኦህዴድ-ኢህአዴግ የተቀላቀሉ ታጋይ በመሆናቸው፣ ከደርግ ውድቀት ቦኋላም በመከላከያ ሰራዊ ውስጥ ከተራ ወታደር ጀምሮ እስከ ኮነሬልነት ማዓርግ በመድረስ አገራቸውን ያገለገሉ፣ በተለይ አገራችን ኢትዮጵያ በግፈኛው የኤርትራ መንግስት በተወረረችበት ወቅት በመዝመት ዜግነታዊ ግዳጃቸው በብቃት የተወጡ፣ በትምህርት ደረጃቸውም እስከ ሶስተኛ ዲግሪ /ዶክትሬት ዲግሪ/ የደረሱ፣ በዕድሜ ደረጃም ገና ወጣት የ42 ዓመት ጎልማሳ በመሆናቸው፣ በስራና በትግል ቆይታቸው ብልህ እና በተለይ አሳምኖ የማሰለፍና የማሰራት ብቃታቸው ከፍተኛ በመሆኑ፣ የስርዓታችን አደጋ የሆነውን ኪራይሰብሳቢነት ለመዋጋት ቁርጠኛ መሆናቸውና የህዝቡ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው በመጠየቃቸው ከፍተኛ ንቅናቄ ይፈጥራሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡ በተለይ ክቡር ጠ/ሚ ዶ/ር አብዪ በሶማሌ፣ በትግራይ እና በአማራ ክልሎች ከህዝብ ጋር ባደረጓቸው ውይይቶች በሰጧቸው መግለጫዎችና ማብራሪያዎች፣ ያልተገባ ቃል ከመግባት በመቆጠብ አንድነት ሰላምና ፍቅር በመስበክ እንዲሁም ኪራይ ሰብሳቢነት መዋጋት ትልቅ ትኩረት የሰጡ ወጥነት ያለው ንግግሮች በማድረጋቸው በህዝቡ ዘንድ ተአማኒነት በማትረፍ ላይ ናቸው፡፡ በተለይ ከአሁን በፊት የነበሩ መሪዎች ያለፈውን የህዝቦች ታሪክ በአደባባይ መንገር ያልተለመደውን አሁን ክቡር ጠ/ሚኒስተሩ በየሄዱበት ክልል ታሪኩ፣ ቋንቋው እና ባህሉ ሲያወድሱለት፣ ህዝቡን ሊጠይቀው የሚፈልገው ጥያቄዎች አስቀድሞ በማወቅ በመግለጫቸው አካተው ማብራሪያ በመስጠታቸው ትልቅ አድናቆት ያተረፉና በህዝቦች ላይ ተስፋ የተጣለባቸው ሆኖዋል፡፡ በተለይ እስካሁን ሊደፈር ያልተቻለውን የተደራጀ የኪራይ ሰብሳቢነት ሰንሰለት ለመበጣጠስ ቁርጠኛ እስከሆኑ ድረስ፣ እንደ ክቡር መሪያችን አቶ መለስ ዜናዊ ዘመን ተሻጋሪ አድናቆት እንደሚቸራቸው ምንም ጥርጥር

የለውም፡፡ በተለይ በአሁኑ ወቅት አገራችን ካለችበት ሁኔታ አንፃር ክቡር ጠቅላይ ሚኒስተር እላይ የተዘረዘሩትን በግላቸው ያላቸውን ብቃት ተጠቅመው በአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር ሳይበረዝ እና ሳይሸራረፍ መምራት ከቻሉ ዳግመኛ የለውጥ መሪ በመሆን አገራችን ወደፊት ማራመድ እንደሚችሉ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡ ፡

# 4 የአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስተር ፈተናና የመፍትሄ አቅጣጫ

አዲሱ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ወደ ስልጣን የመጡበት ወቅት በጣም ፈታኝ የሚያደርገው የኢህአዴግ ኣባል ድርጅቶች ከቆሙለት መስመር ውጭ በዝቅጠት ጎዳና ቀላል የማይባል ርቀት የተጓዙበት እና የህዝቡን የልማት ጥማት በሚፈለገው መጠን ማርካት ባልቻሉበት፣ በተለይ ወጣቱ ትውልድ ስርዓቱ በፈጠረለት ዕድል ተጠቅሞ በሰፊ የመማር ዕድል ያገኘ ቢሆንም ትምህርትና ስልጠናው አጠናቅቆ ሲያበቃ የስራ ዕድል በማግኘት በኩል ከፍተኛ ችግር ባለበት ጊዜ በመመረጣቸው የስልጣን ቆይታቸው እልህ አስጨራሽ ትግል ስለሚጠይቅ ትልቅ ፈተና ነው፡፡ በተለይ በአሁኑ ሰዓት በአመራሩ በኩል እየታየ ያለው የጎራ መደበላለቅ፣ የትምክህትና ጠባብ አመለካከቶች መንሰራፋት፣ የህዝቡ የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄና የፈፃሚው አካል በተለይ የሲቪል ሰርቪሱ ብቃት አለመመጣጠን የችግሩ ኣሳሳቢነት ጎልቶ እንዲታይ ያደርጓል፡፡ ይህን ፈተና መቋቋም የሚቻለው ግን ጥልቅ ተሃድሶው በተገቢው መንገድ ህዝብን ባሳተፈ መልኩ ማስቀጠል ሲቻል ብቻ ነው፡፡ ስለዚ የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስተር በሚቀጥሉት 100 ቀናት ትኩረት ሰጥተው መሄድ አለባቸው የምለው

- በመጀመሪያ ደረጃ በጥልቅ ተሃድሶ ውስጥ ራስን በማስገባት በአብዮታዊ ዴሞክራሲ እሴቶችና መርሆዎች ባጠቃላይ የራስን ቁመና መፈተሽና በንፁህ ህሊና ራስን ሂስ ማድረግ፤
- ቀጥሎ ድርጅትዎን (ኦህዴድ) በተመሳሳይ መንገድ በመፈተሽ ወደ ዳግም ጥልቅ ተሃድሶ በማስገባት ድርጅትን የማጥራት ስራ ባፋጣኝ መስራት፣
- ቀጥሎ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችን የዳግም ጥልቅ ተሃድሶ እንቅስቃሴ ያለበትን ደረጃ በመገምገም ወጥነት ያለው አካሄድ እንዲኖር የማድረግ እና በድርጅቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ወደ ትክክለኛው ቦታው የመመለስ ስራ መስራት ነው፡፡

ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ተግባራዊ ማድረግ ከቻሉ፣ 8 ሚሊዮን የልማት ሰራዊት አመራር በአንድ ጊዜ ከአንድ ማእከል በጥብቅ ዲስፕሊን ማዝመት ስለሚችሉ ህዝቡ የሚያነሳቸው ተቀጣጣይ ጥያቄዎችና ዘላቂ የልማት ጥማቶችን በተፈለገው ማሳካት ይቻላል፡፡ ይህን ማድረግ ካልተቻለ ግን የተበተነ ሰራዊት ወይም ያልተደራጀና የጋራ ዓላማ ያልያዘ ሰራዊት መምራት በጣም አስቸጋሪ ያደርጓል፡፡ በርግጠኝነት ማለት የሚቻለው ነገር ቢኖር ጥልቅ የሃድሰው ተቀጣጥሎ እንዳይ ሄድ ጥቂት ኪራይ ሰብሳቢዎች በተደራጀም በተናጠልም ባለና በሌለ

ኃይላቸው ለማደናቀፍ እንደሚጥሩ የታወቀ ቢሆንም 99% የልማት ሰራዊቱ ግን የተሃድሶው መቀጣጠል በጉጉት እንደሚጠብቀው ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ስለዚ የጠቅላይ ሚኒስተር ቆራጥነት ወሳኝ ሚና አለው፡፡

# 5 ማጠቃለያ

አገራችን ኢትዮጵያ ለዘመናት የኋልዮሽ ጉዞ ስትጓዝ ከቆየች ቦኋላ በስተመጨረሻ ብሶት የወለደው የኢህአዴግ ሰራዊት ከ17 ዓመት መራራ የትጥቅ ትግል ቦኋላ የድህነት ዘበኛ የነበረውን ፀረ ህዝብና ፀረ ዴሞክራሶያዊ የደርግ ስርዓት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተደምስሶ በምትኩ ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ተተክሎ እነሆ አገራችን ኢትዮጵያ ከብተና አፋፍ ወጥታ ፈጣን፣ ፍትሃዊና ዘለቄታ ያለው ልማት በማረጋገጥ በዓለማችን ከሚጠቀሱ ጥቂት አገራት አንዷ ለመሆን በቅታለች፡፡ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባተ በኩልም ኢትዮጵያ ከደርግ ውድቀት ቦኋላ ዘመናዊና ዴሞክራሲያዊ የሚባል ህገመንግስት በህዝብ ተሳትፎ ኣፀድቃ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ 5 ተከታታይ ነፃ፣ ዴሞክራሲያዊና ተኣማኒነት ያተረፈ የህዝብ ምርጫዎች በማስተናገድ ህዝባዊ መንግስት ለመመስረት በቅታለች፡፡ በዚህ የአገራችን የ43 ዓመታት የድልና የስኬት ጉዞ ጀርባ እንደ ድርጅት ኢህአዴግ ሲወሳ እንደ ፕሮግራም ደግሞ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም ልማታዊ ዴሞክራሲ የሚጠቀስ ነው፡፡

ይሁንና 43 የትግልና የድል ዓመታትም ቢሆኑ ከባድ መስዋእትነት የተከፈለበት እና ከባድ ፈተናዎች የታለፈበት ምእራፎች ነበሩት፡፡ ኢህአዴግ በትግል ታሪኩ እስከ አሁን ድረስ ሶስት ፈታኝና ድርጅቱን ለብተና ዳርገው የነበሩ የመበስበስ አደጋዎች የተጋረጡበት ሲሆን ሁለቱም በድል እና በስኬት በማለፍ ተሃድሶዎቹን ተከትሎ ከፍተኛ የህዝብ መነሳሳት በመፍጠር ተአምራዊ ድል የተመዘገበበት ሁኔታ ነበር የተፈጠረው፡፡ የመጀመሪያው ተሃድሶ ውጤት ሲታይ ደርግን ያክል ግዙፍ አፋኝ ስርዓት ከነ ሙሉ ትጥቁ በ5 ዓመታት ውስጥ ለመድምሰስ ያበቃው የተሃድሶው መስመር ነበር፤ የሁለተኛው ተሃድሶ ውጤት በሚታይበት ጊዜም ከድሪቶ አመለካከት በመውጣት አገራችን ወደ ፈጣን የዕድገት ምህዋር በማስገባት ለተከታታይ 15 ዓመታት ከፍተኛ እድገት ተመዝግበዋል፡፡ ሶስተኛው ተሃድሶ (ጥልቅ ተሃድሶ) ግን ካለፉት ሁለቱ ተሃድሶዎች በተለየ ሁኔታ አሁንም ገና ብቁ መሪ ወይም የተሃድሶ መሃንዲስ ያልተገኘለት በቋፍ ላይ ያለ ተሃድሶ ነው፡፡

ከአሁን በፊት በብዙ ፅሁፎች ለመግለፅ እንደተሞከረ፣ ኢትዮጵያ አገራችን ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ውጭ ያለ መንገድ የጥፋት መንገድ እንደሆነ በቲኦሪ ደረጃ ለመግለፅ ተሞክረዋል፡፡ አሁን ዝቅጠቱና የመበስበስ አደጋው በተጨባጭ ያሳየን ነገር ቢኖር ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ዝንፍ ማለት ከተጀመረ ምን ያክል አደገኛ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ እላይ እንደተገለፀው የዘንድሮ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ምርጫ ከኢህአዴጋዊ ባህልና ልምድ ውጭ፣

የቡዱናዊ አሰራር ሽታ ያለበት በአጠቃላይ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ እሴቶች ወጣ ያሉ ክስተቶች የታዩበት የተካሄደ በመሆኑ በአጋር ድርጅቶች የሙብት ጥያቄ እስከ መጫር ደርሷል፣፡፡ ለመጥቀስ ያክል ጠቅላይ ሚኒስተርነት በብሄር ከሆነ ለምን እኛስ ኣይመለከትንም እንዴ? እኛ ኢትዮጵያዊያን አይደለንም ወይ? የአገር መሪ ለመሆን የግድ የትግራይ የአማራ፣ የኦሮሞና የደቡብ ተወላጅ መሆን ነው ወይ? የሚሉ ከአሁን በፊት ተነስተው የማያውቁ አደገኛ አመለካከቶች መውጣት ተጀምሯል፡፡ እነዚህ አመለካከቶች ጎልቶው መውጣት የቻሉት በገዢው ፓርቲ፣ የኣብዮታዊ ዴሞክራሲ እምነቶችን ሲሸረሸሩ በመታየታቸው ነው፡፡ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እምነት በሰረፀበት ጊዜ ይቅርና የአገራችን ብሄርና ዘር ቆጠራ፤ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር በፅናት የጨበጠ እስካለ ድረስ ግለሰባዊ-ማንነት ብዙም ትኩረት የሚሰጠው አልነበረም፡፡ የዘር ቆጠራ ወይም ልክ እንደ የጎሳ አለቃ ምርጫ በየተራ ስልጣንን መጠበቅ በኢህአዴግ ውስጥ ታይቶ አይታወቅም፡፡

ስለዚ አሁን የደረሰብንን አደጋ ዋና ዋና ምክንያትና ምንጩ በጥልቅ ተሃድሶ ሰነድ በግልፅ ተለይቶ ተቀምጧል፡፡ ህዝቡም እንዲወያይበት እየተደረገ ነው፡፡ ይህን ግምገማ ሰነድ በደንብ በመውሰድ ወደ ውጭ በመቀሰር ሳይሆን የራሴን ችግር እራሴ የፈጠርኩት ነው ብሎ በመውሰድ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የማዳን ስራ መስራት አለብን፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የማዳን ስራ ኢትዮጵያን የማዳን ስራ ነው፡፡ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ጥልቅ ተሃድሶው ወደታች ወደ ህዝቡ ማውረድ አለባቸው፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ የብዙሃነት አገር መሆንዋ የማይካድ ተፈጥሮ የለገሳት ፀጋ ነው፡፡ ይህ ፀጋ ሃይል/ጉልበት ሆኖ ሊቀጥል ከተፈለገ ብሁሃነትን በአግባቡ ማስተናገድ የሚያስችል ስርዓት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ስርዓት ደግሞ ብዙሃነትን የተቀበለ፣ በእኩል ማስተናገድ የሚችል፣ እኩል እውቅና የሚሰጥ፣ እኩል ሙብት የሚሰጥና የማያበላልጥ፣ መቻቻልን የሚሰብክ ሲሆን ነው፡፡ ይህን ማሟላት የሚችል ደግሞ የቡድን ሙብት የተቀበለ ብቻ ነው፡፡ የቡድን ሙብት መቀበል የማይችል አመለካከት ይህን ማሟላት አይችልም፡፡ በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ይህ ማድረግ የሚችል ፕሮግራም አብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም ልማታዊ ዴሞክራሲ ብቻና ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያ ውስጥ ህጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ከሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ የቡድን ሙብት በተሟላ መልኩ የሚቀበል ብቸኛው ድርጅት ኢህአዴግ እና አጋር ድርጅቶች ብቻ ናቸው የተቀሩት ከ90% በላይ የፖለቲካ ድርጅቶች ግን ይኸንን በጥብቅ የሚቃወሙ ናቸው፡፡ አሁን የጠ/ሚ ምርጫ ተከትሎ ከተቋዋሚና ተፎካካሪ ድርጅቶች እየጎረፈ ያለው አድናቆትና ሙገሳ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመራችን ላይ ያነጣጠረ ሚሳይል እንዳይሆን በንቃት መከታተል ያስፈልጋል፡፡ ከሁሉም የሚገርመው የህዝቦች እኩልነት ያረጋገጠው ዴሞክራሲያዊ ህገመንግስታችን 23 ዓመት ሙሉ ሳይሰለቹ ሕገ-አራዊት በማለት ሲያጥላሉ የነበሩት ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ሳይቀር ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስተር ዶ/ር አብዪ አሕመድ እና ለኦሮምያ ርእሰ መስተዳድር ክቡር አቶ ለማ መገርሳ በለውጥ ሃዋርያነታቸው ሲያሞግሷቸው ይውላሉ፡፡ ስለዚህ ሊበሏት የፈለጉ

እንስሳ ..... እንደሚባለው ነውና ተገቢ ካልሆነ አቅጣጫ የሚመጡ ፕሮፖጋንዳዎች በትኩረትና በንቃት መከታተልና መስመራችንን ከሰርጎ ገቦች ጥቃት መመከት ይጠበቅብናል፡፡

በልማት በኩል ሲታይም፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች እያነሱት ያለውን ጥያቄ የልማት ተጠቃሚነት ጥያቄ፣ በልማት የመሳተፍ ጥያቄ፣ የፍትሃዊ ተጠቃሚነት ጥያቄ፣ የመሰረተ ልማት ጥያቄ፣ ባፋጣኝ መልስ ማግኘት የሚችለው በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም ልማታዊ ዴሞክራሲ መስመር ብቻ ነው፡፡ ከልማታዊ ዴሞክራሲ ውጭ ያሉ ፕሮግራሞች ሁሉ መንግስት በሕግ ማስከበርና ዳርድንበር በማስጠበቅ ዙርያ ብቻ እንዲታጠር በማድረግ፣ የመንግስት እጅ አሳስረው በመያዝ፣ የህዝቡ የልማት ጥያቄ በዘገምተኛው የግሉ ዘርፍ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ መፍትሄ እንዲያገኝ የሚያደርጉ በመሆናቸው ነው ልማታዊ ዴሞክራሲ በአገራችን ብቸኛው ፈጣን የልማት ምላሽ የሚሰጥ ፕሮግራም ነው የምንለው፡፡ ጠንካራ አንድነት ከመፍጠር አኳያ ሲታይም አገራችን ኢትዮጵያ በ21ኛው ክፍለዘመን ***<u>አንድነቷና እኩልነቷን</u>*** አስጠብቆ ማስቀጠል የሚችል ብቸኛው ፕሮግራም ወይም አመለካከት አብዮታዊ ዴሞክራሲ በሌላ አጠራር ልማታዊ ዴሞክራሲ ብቻ ነው፡፡ ይህ መስመር ለኛ ለኢትዮጵያውያን ብቻ የሚጠቅም ሳይሆን ለማንኛውም ጭቁን ህዝቦች ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ባፋጣኝ ማላቀቅ የሚችል ፍቱን መስመር ነው፡፡ ***<u>ስለዚ ይህ ብቸኛው መስመር የማዳን እና ያለማዳን ጉዳይ ኢህአዴግን የማዳንና ያለማዳን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ውዷ አገራችን የማዳንና ያለማዳን ጉዳይ ነው፡፡</u>***

የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም የልማታዊ ዴሞክራሲ ጉዳይ ከፖለቲካዊ ድርጅት ጉዳይ በላይ ነው፡፡ ስለዚ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የማዳን ጉዳይ ለኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ኮር አመራር ብቻ መሰጠት የለበትም፡፡ የዚህ መስመር የማዳንና የመጠበቅ ጉዳይ የ8 ሚልዮን የኢህአዴግ ግንባር ቀደም እና የሁሉም አጋር ድርጅቶች እንዲሁም የምልኣተ ህዝቡ ጉዳይ ተደርጎ መወሰድ አለበት፡፡ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስተር ዶ/ር አብዪ አሕመድ ባደረጓቸው ጉብኝቶች ላይ ይነሱ የነበሩ ጥያቄዎች ሁሉም ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር ውጭ ለመመለስ መሞከር በጣም አደገኛ ይሆናል፡፡ እዚህ ላይ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር ውጭ ለመመለስ አንድ እርምጃ መንቀሳቀስ ማለት አገራችን የማፈራረስ አንድ እርምጃ መራመድ ማለት ነው፡፡ የዚች አገር ጥያቄዎች በአግባቡ (ማለትም ዴሞክራሲያዊ፣ ፍትሃዊ፣ ሰላማዊና በጣም ፈጣን በሆነ መንገድ) መፍታት የሚችለው ይህ መስመር ብቻና ብቻ ነው፡፡

ስለዚህ መስመሩን አስጠብቆ ማስቀጠል የሚቻለው ደግሞ፣ በኢህአዴግ ውስጥ ተንሰራፍቶ ያለው የኪራይ ሰብሳቢነት በሽታ መቅረፍ ሲቻል ነው፡፡ ይህን ትግል ውስብስብ የሚያደርገው ጉዳይ በዚህ በሽታ የተለከፈው ሃይል ዋና የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አቀንቃኝ መስሎ የሚታየው አስመሳይ በመሆኑ በመለየት ላይ ብልሃት ያስፈልጓል፡፡ ኪራይ ሰብሳቢነት የራሱ የሆነ መለያ ሃይማኖት፣ ብሄር፣ ፆታ የለውም፡፡ ይህንን መለያ ወይም

ታርጋ የሚሰጥ ካለ ራሱ ኪራይ ሰብሳቢ ነው፡፡ ኪራይ ሰብሳቢነትም ኮንትሮባንድነትም የኛ ድርጅት፣ የኛ ብሄር፣ የኛ ክልል አይነካም በማለት፣ የብሄር ወይም የጎሳ መልክ እንዲኖረው ለማስመሰል መጣር የራስን የኪራይ ሰብሳቢነት ችግር ለመደበቅ ካልሆነ በስተቀር አብዮታዊነት አይገልፅም፣ የለውጥ ሃዋርያ አያስብልም፡፡ በኪራይ ሰብሳቢነት የሚጠቀም ህዝብም፣ ብሄርም የለም፣ በኪራይ ሰብሳቢነት የሚጠቀም ካለ በኪራይ ሰብሳቢነት የተዘፈቀ ግለሰብ ብቻ ነው፡፡ ስለዚ ኪራይ ሰብሳቢነት ለመዋጋት የምናደርገው ትግል ሊያደናቅፈን የሚችል ከኪራይ ሰብሳቢ ንኪኪ ያለው፣ ኮንትሮባንድ ንክኪ ያለው ጥቅሙ የጎደለበት ግለሰብ መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ ለዚህ በሽታ ብሄር ወይም የህዝብን ማንነት ጋር ደማምሮ መታገል ፀረ ህዝብነት እንጂ ፀረ ኪራይ ሰብሳቢነት አይደለም፡፡ ኪራይ ሰብሳቢነት የትግራይ ህዝብ፣ የአማራ ህዝብ፣ የኦሮሞ ህዝብ የሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦች ጠላት መሆኑ መጠራጠር አይገባም፡፡ ቆራጥ አመራር እስከተገኘ ድረስ በኪራይ ሰብሳቢነት ትግል ዙርያ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከጫፍ ጫፍ ንቅናቄ መፍጠር ይቻላል፡፡ በአንዳንድ ክልሎች የሚታይ ያለው የኪራይ ሰብሳቢነት ችግር ከብሄር፣ ጎሳ ወይም ክልል ጋር በማያያዝ የለውጥ ሃዋርያ ለመምሰል የሚደረግ ሙከራ በጣም አደገኛና ኪራይ ሰብሳቢነት ከስረመሰረቱ እንዳይነቀል ለመከላከል የሚሸረብ ሴራ ከመሆን አያልፍም፡፡

ኢህአዴግ ባፋጣኝ ወደ ድሮው አብዮታዊ ዴሞክራሲ እሴቶችና መስመር መመለስ አለበት፡፡ እስከአሁን የተገኙ አመርቂ ድሎችን አስጠብቀን መሄድ የምንችለው ይህን መስመር አጥብቀን እስከያዝን ድረስ ነው፡፡ ኢህአዴግ ወደ ችግር የገባው አብዮታዊ ዴሞክራሲ አጥብቆ በመያዙ ሳይሆን ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር ማፈንገጥ በመጀመሩ ነው፡፡ ስለዚህ በአንዳንድ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች እና በአንዳንድ አመራሮች፣ የህዝብን ጥያቄ ለመመለስ በሚል ሰበብ እየታየ ያለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም የልማታዊ ዴሞክራሲ መስመር የመሸርሸር አባዜ በፅናት ልንታገለው ይገባል፡፡